# "ደብተራ ፍጽምት ዘጳውሊ"

ከመምህር ሀብተማርያም ተድላ

በዓለም ተወዳዳሪ የማይገኝለት ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዓለ ዕርገት ሲዘምር "ደብተራ ፍጽምት ዘጳውሎ ወማኅደሩ በጽድቅ ዘገብራ ከሃሊ፤ ፈለሰት እምዘ ይበሊ ኀበ ኢይበሊ፤ በመሰንቆሁ እንዘ የኀሊ ዳዊት አቡሃ ዘወልዳ ወዓሊ" ይላል፡፡

ይህም ወደ አማርኛ ሲተረጎም "ደብተራ"ማለት ድንኳን፣ ማደርያ፣ መኖርያ...ማለት ሲሆን በብዛትም "ደባትር"ማለት ይቻላል፡፡ የዜማና የቅኔ ባለሙያ "ደብተራ"ተብሎ ይጠራል፡፡ የዜማና የቅኔ መኖርያ /ባለሙያ/መባሉ ነው፡፡ ታዲያ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን "ደብተራ ፍጽምት ዘጳውሊ"ፍጽምት የጳውሎስ ድንኳን ሲላት ምን ማለቱ ይሆን?ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን በጻፈው መልዕክቱ ምዕ.9፡11"ክርስቶስ አሁን ስላሉት መልካም ነገሮች ሊቀ ካህናት ሆኖ በመጣ ጊዜ በሰው እጅ ወዳልተሠራችው፤ ከዚህ ፍጥረት ወዳልሆነቻው ታላቅና ፍጽምት ድንኳን ገባ"በማለት ያስተላለፈውን መልእክት ጠቅሶ "ደብተራ ፍጽምት ዘጳውሊ"ትንቢቱና ምሳሌው የተፈጸመላት የጳውሎስ ድንኳን ድንግል ማርያም ሁሉም ማድረግ የሚችል አምላክ የልዑል የእግዚአብሔር ቃል ማደርያ በእውነት ያደረጋት የልጅዋ አገልጋይ የሆነ አባትዋ ዳዊት በመሰንቆው እየዘመረ ከዚህ ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም ተሻገረች፣ ኼደች፣ ዐረገች... በማለት ነው የሚዘምረው፡፡ /ዋዜማ እግዚአብሔር ነግሠ/ ይህም አዲስ ፈጠራ ሳይሆን ቀደም ብሎ በታላቁ የእግዚአብሔር ወዳጅ ነቢየ እስራኤል ሙሴ ዘመን የተዘጋጀ የታቦተ ሕግ የጽላተ ኪዳን መኖርያ ቅድስተ ቅዱሳን "ደብተራ"ተብሎ ነበር የሚጠራው፡፡ ይህም በአካል ማደርያው ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር የመረጣት የድንግል ማርያም ምሳሌ ስለ ነበረ ጊዜው ሲደርስ የእግዚአብሔር ቃል በማኅፀንዋ አደረ፡፡ አምላክ ሰው ሆነ፤ ሰው አምላክ ሆነ፤ ተዋሐደ፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ኤፍሬም፡-"አንቲ ውእቱ ደብተራ እንተ ተሰመይኪ ቅድስተ ቅዱሳን ወውስቴታ ጽላተ ኪዳን"በውስጧ ጽላተ ኪዳን የቃል ኪዳን ታቦት /ኢየሱስ ክርስቶስ/ያለባት ቅድስተ ቅዱሳን ተብላ የምትጠራ የእግዚአብሔር ቃል ማደርያ ድንኳን አንቺ ነሽ" በማለት ይመሰክርላታል፡፡ ውዳሴ ማርያም ዘቀዳሚት የሐዋ.7፡ 44፡54፤ ዘጸ.26፡1-37፤ ዕብ. 8፡5-13፤

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቀደም ብሎ ከአምላክ የተሰጠው ተስፋና በአባቶች ነቢያት የተነገረው ትንቢት በዚህች ቅድስት ድንግል ማርያም መፈጸሙን ሲያበሥር "ወአመ ወጽሐ ዕድሜሁ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ ውስተ ዓለም"ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም ላከ ወተወልደ "እምብእሲት" ከሴትም ተወለደ.... በማለት ከላይ በድንኳን የመሰለውን አሁን ከዚህ ላይ በከርሥ ብእሲት አድሮ ሰው ሆኖ መወለዱን በግልጽ ያስረዳል፡፡ ገላ. 4.4. ፤ ማር. 1፡15 ፤ ሉቃ. 2፡27፤ ዮሐ. 1፡14

ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ ስንል ምን ማለታችን ይሆን? ማንና ማን የተቀጣጠሩበት ቀጠሮ ይሆን?... ቅዱሳት መጻሕፍትን ብንመረምር መልሱን በየገጹ እናገኛለን፡፡ ስለዚህ ቀጠሮ አጣርቶ ማወቅ የፈለገ ማንኛውም ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍትን ቢመረምር የጉዳዩ መነሻና መድረሻ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆና ያገኛታል፡፡
ይኸውም፤

**1.** በኃሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምበለትከ

ዓለማትን የፈጠረ፣ ሁሉም ማድረግ የሚችል ...አምላክ ፍጥረታትን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ ሰውን በአርአያውና በአምሳሉ አዋቂና ተመራማሪ አድርጎ ፈጠረው፡፡ ወንድና ሴትም አደረጋቸው፡፡ በአየር የሚበረውን በምድር የሚሽከረከረውንን በባሕር የሚርመሰመሰውን ፍጥረት ሁሉ እንዲገዙም ሙሉ ስልጣን ሰጥቶ በገነት አኖራቸው፡፡

አምላክ እንደመሆኑ መጠን ትዕዛዙን ጠብቀው ይኖሩ ዘንድ አንዲት ትዕዛዝ ሰጣቸው፡፡ እነሱ ግን አንዲት ትዕዛዝ መጠበቅ አቃታቸውና እባብን መስሎ በመጣ በዲያብሎስ ምክር የፈጣሪያቸውን ትዕዛዝ ጣሱ፤ አፈራረሱ፡፡ ስለዚህ ከተሾሙባት ገነት ተባረሩና በአንጻረ ገነት ሆነው አለቀሱ፡፡ ንስሐ ገቡ ዘፍ. 3፡1-2፡፡

የሐጢአተኛ መመለሱን እንጂ ሞቱን የማይፈልግ ርህሩህ አምላኽ ለቅሶአቸውን ሰማ፤ ሐዘናቸውም ተመለከተና "በኃሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምበለትከ"ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ እወለዳለሁ፤ ወእድሕክ ውስተመርኅብከ፣ ወእትቤዘወከ በሞትየ ወበመስቀልየ፣ በአደባባይ እድኀለሁ፤ ሙቼ ተሰቅየም አድንሀለሁ፣ ቤዛ እሆንሃለሁ በማለት ለአዳም ቃል ገባለት፤ በዚህም ቀጠሮ ሰጠው፡፡ (the forgotten books of Eden. chapter 3 p.6)

**2.** አባታችን አዳም ይህንን ሲሰማ እጅግ ደነገጠ፤ እግዚአብሔር አምላክ አምስት ቀን ተኩል ያለው አባባል አልተረዳውምና ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ዓለም የሚያልፍ ስለመሰለው ይበልጥ ተጨነቀ፤ የዚህ የአምስት ቀን ተኩል ምስጢር እንዲገለጽለትም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤ አለቀሰ፡፡በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረው እግዚአብሔርም ጩኸቱም ሰማና በርህራሄ ዓይኑ ተመለከተው፡፡ ስለዚህም አምስት ቀን ተኩል የተባለው 5500 ዘመን መሆኑን ገልጾ ይህ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም በመጀመርያ የፈጠረውንና በለመለመች ገነት ያኖረውን፤ በኋላ ትዕዛዙን በጣሰ ጊዜ መልአኩን ልኮ ከገነት ያባረረውን እንደገና በከፍተኛ ሐዘን ላይ ወድቆ ለሞት ደርሶ በነበረበት ጊዜ ከወደቀበት ያስነሳው የእግዚአብሔር ቃል ከልጅ ልጁ ተወልዶ እንደሚያድነው አበሰረውና ቀጠረው፡፡ /መጽሐፈ አዳም/፡፡

**3.** የይቅርታ ባለቤት እግዚአብሔር አምላኽ ሄዋንን ባሳሳተ እባብ ላይ ፍርድ በሰጠበት ጊዜ በአንተና በሴቲቱ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አስነሳለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ተረከዙን ትነክሳለህ ብሎታል፡፡ ዘፍ. 3፡15፤ ኢሳ. 7፡ 14፤ ዮሐ. 8፡44 ፤ ሮሜ. 16፡20 ፤ ራዕ. 12፡17፤

ይህም በቀራንዮ በዕለተ ዓርብ ሲፈጸም ታይቶአል፡፡ የእባብ ዘር የተባለ ዲያብሎስ በአይሁድ ልቡና አድሮ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስያዘ፤ በመስቀል አሰቅሎ እጅ እግሩን በብረት አስቸነከረ...ማለት ሰኰናውን ነከሰ፡፡ ዘርአ ለብእሲት የተባለው ጌታ ኢየሱስም በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ የእባብ /የዲያብሎስን/ ራስ ቀጥቅጦ አዳምና ሄዋንን ከነዘር መንዘራቸው ነጻ አወጣ፡፡ 1ጴጥ. 3፡18-22

እንግዲህ አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን የነበራቸው የመዳም ተስፋ ቀጥሮ ባጭሩ ይህንን የሚመስል ሲሆን በአባቶች ነቢያት የተነገረ ትንቢትም እንደሚከተለው በመጠኑ እናያለን፡፡
ለአባታችን ለአብርሃም ከእግዚአብሔር አምላክ የተነገረ ታላቅ ተስፋ "በዘርእከ ይትባረኩ ኩሎሙ አሕዛበ ምድር"የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ ተብሎለታል፡፡ ይህም ማለት ከአብርሃም ዘር ከተገኘች ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሚወለደው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና መጠመቅ በጥምቀት መወለድ መሆኑ አያከራክርም ማቴ. 11፡3-9 ፤ ሉቃ. 3፡8 ዮሐ. 3፡36፤

ሊቁ አባ ሕርያቆስ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም "ታቦት ዘኖኅ አንተ ባቲ ድኅነ እምአኩይ አይኅ"ኖኅ ከክፉ የጥፋት ውኃ የዳነብሽ ታቦት፣ ማደርያ፣ መኖርያ፣ መከለያ፣ ድንኳን /መርከብ/ ነሽ ይላታል፡፡
ቀጥሎም "ጽላት ዘሙሴ ዕፀ ጸጦስ ዘሲና"በማለት ያወድሳታል ምን ማለቱ ይሆን?የጥፋት ውኃ የወረደውና ኖኅ ታቦት ወደተባለችው መርከብ የገባው በ1661ዓ.ዓ የ601ዓመት ዕድሜ በነበረበት ዘመን መሆኑን እንረዳለን" ዘፍ. 5፡1፤ 8፡13፡፡
እንደዚሁም ሙሴ ወደ ምድያም የሸሸውና በኃቅለ ሲና ሐመልማል ከነበልባል፤ ነበልባል፤ ከሐመልማል ተዋሕዶ ያየው በ3793ዓ.ዓ ነበር፡፡ እመቤታችን የተወለደችው ግን በ5485ዓ.ዓ መሆኑ ግልጽ ነው አያከራክርም፡፡ ታዲያ ከመወለድዋ በፊት በሺሕ የሚቈጠሩ ዘመናት እያሉ በሌለችበት እንዴት ኖኅን ከጥፋት ውኃ አዳነች....እንዴትስ ለሙሴ በሐመልማል ተገለጠች የሙሴ ጽላትስ እንዴጽ ተባለች የሚል ጥያቄ የሚያነሱ ሰዎች ይኖሩ ይሆን? በዚህ ባይጨነቁ ከዚህ የበለጠ አለና፡፡

**4.** በዓለም ተመሳሳይ የማይገኝለት ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድ በበኩሉ

**ሀ**/"ዘእንበለ ይትፈጠር ሰማይ ወምድር፤ ወዘእንበለ ትሣረር ምድረ ገነት ሀለወት ስብሕት፣ ቅድስት ወቡርክት ይእቲ ማርያም፣ እንቲ ተሰምየት ሰንበተ ክርስቲያን"ሰማይና ምድር ሳይፈጠር የገነትም ምድር ሳትመሠረት ሰንበተ ክርስቲያን /የክርስቲያን ዕረፍት/ተብላ የምትጠራ፤ የተመሰገነች የተለየችና የተባረከች ማርያም ነበረች፤
**ለ**/"ማርያምሰ ተሐቱ እምትካት ውስተ ከርሡ ለአዳም ከመ ባሕርይ ፀዓዳ"... ማርያምስ ከጥንት ጀምሮ በአዳም አካል ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ስታበራ ትኖራለች ብሎአል፡፡ (ድጓ ዘኀደር ጽዮን)

እኮ ታዲያ እነዚህ አባቶች እመቤታችን ከአባትዋ ከኢየቄምና ከእናትዋ ከሐና በ5485ዓ.ዓ መወለድዋ እየታወቀ እንዴት ዓለም ሳይፈጠር ነበረች ይላሉ?...መልሱ በጣም ቀላል ነው፤ መጀመርያና መጨረሻ የሌለው፤ በዚህ ጊዜ ተነሣ፤ በዚህ ጊዜ ያልፋል የማይባል ዘመን የማይቆጠርለት ቀዳማዊ ወደሐራዊ አምላክ ሁሉም ነገር ከመሆኑ በፊት እንደሚሆን ያውቃልና አዳምና ሔዋን ትእዛዙን ከመጣሳቸው በፊት እንደሚጥሱና እንደሚፈረድባቸው፣ ንስሐ እንደሚገቡና እንደሚመለሱም ዐውቆ ወደ ቀደመ ክብራቸው ለመመለስ መሣርያ አድርጐ ያዘጋጀ ስለሆነ ገና በአዳም አካል ውስጥ ባለች እንደ ነጭ ዕንቁ ታበራ ነበር፡፡ ገና ሰማይና ምድር ሳይፈጠሩም በሕሊና አምላክ ነበረች ማለት ነው፡፡

እስቲ እንግዲህ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ታቦት ወደ ተባለችበት እንመላለስና በማስተዋል እንመልከት፡፡ "ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኩለሄ ዘግቡር እም ዕፀ ዘኢይነቅዝ"...ከማይነቅዝ ዕንጨት የተሠራ በውጭም በውስጥም በወርቅ የተለበጠ ታቦት የእግዚአብሔር ቃል ምሳሌ ይሆናል፡፡ ለመሆኑ ታቦት ማለት ምን ማለት ይሆን?ታቦት፡-ማለት ቤተ አደረ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ዘር ሲሆን መኖርያ፣ ማደርያ ፣የሚኖበት ድንኳን፤ ሢጥን ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፈበት ጽላት የሚኖርበት፣ የእግዚአብሔር ቃል ማደርያ ማኅደረ እግዚአብሔር ማለት ሲሆን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም የእግዚአብሔር ቃል ማደርያ ስለሆነች ታቦት ተብላለች፡፡ ነቢዩ ሙሴ በኃቅለ ሲና ነበልባል ከሐመልማል፤ ሐመልማል ከነበልባል ተዋሕዶ እሳቱ ሐመልማሉን ሳያቃጥል፤ ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳይጠፋ ተመለከተ፡፡ ይህም ሙሴ የእግዚአብሔር ምርጥ ታላቅ ነቢይ ስለሆነ በነበልባል የተመሰለው መለኮት በሐመልማል ከተመሰለችው ከድንግል ማርያም ማኅፀን አድሮ ሥጋ መልበሱንና ፍፁም ሰው መሆኑን ነበር የተመለከተው፡፡

1. የሙሴ ጽላት ስለመባልዋ ልዑል እግዚአብሔር በቅዱስ ፈቃዱ እስራኤልን ከግብፃውያን ባርነት አላቅቆ ነፃ ካስወጣ በኋላ ወዳጁን ሙሴን ጠርቶ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል ከፍታው አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ታቦት ከግራር ዕንጨት እንዲሠሩ አድርግ የምሰጥህንም ምስክር በታቦቱ ውስጥ አኑር ብሎታል፡፡ ዘጸ. 25፡10-23፡፡
በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተሠራው የእግዚአብሔር ማደርያ ታቦት ሲሆን በእግዚአብሔር እጅ የተጻፈ ዐሥር ትእዛዛት የሚኖርበት ጽላትም የእግዚአብሔር ቃል ማደርያ የሆነችው የድንግል ማርያም ምሳሌ ስለሆነ ነው፡፡

2. የአሮን በትር ስለመባልዋ የአሮን በትር ሳይተክሉአት ተተክላ፤ ውኃ ሳያጠጧት ለምልማ፤ አብባ፣ አፍርታ እንደተገኘች እመቤታችንም ያለ ዘርኢ ብእሲ በድንግልና የእግዚአብሔርን ቃል ጸንሳ በድንግልና ወልዳለችና፡፡ ዘኍ. 17፡8፤ ዕብ.9፡4፡፡

3. የሕዝቅኤል ቤተመቅደስ፤ "ያ ሰው ከምሥራቅ ትዩዩ ወደ ሆነው ወደ መቅደሱ በር መልሶ አመጣኝ፤ ተዘግቶም ነበር፤ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ ይህ በር እንደተዘጋ ይኖራል እንጂ አይከፍትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና አለኝ" ይላል ሕዝ. 44፡1-5 ይህም ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለአለማዊ ድንግልና የተነገረ ምሳሌ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ሉቃ.1፡35-35፤ ማር.1፡24፤ ማቴ.1፡18፤

## <u>የእመቤታችን ሐረገ ትውልድ</u>

ከላይ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው እመቤታችን ቅድስት ደንግል ማርያም ከጥንት ጀምሮ በአዳም አካል እንደ ነጭ ዕንቁ ስታበራ ከአዳም እስከ ኖኅ፤ ከኖኅ እስከ አብርሃም፤ ከአብርሃም እስከ ዳዊት፤ ከዳዊት እስከ ኢያቄምና ሐና መድረስዋ ክብረ ነገሥት በእንተ ብካያ ሰሎሞንና በእንተ መድኃኒትነ ማርያም የሚሉትን 67 እና 68 ክፍሎች መመልከት ይቻላል፡፡
የእመቤታችን አባት ኢያቄምና እናትዋ ሐና በእግዚአብሔር ፊት የዋሃንና ስሕተት የማይታይባቸው ደጋግ ሰዎች ነበሩ ሀብታቸው በሦስት ክፍል የተመደበ ነበር፡፡

1ኛው ክፍል ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት
2ኛው ክፍል ለድሆችና እንግዶች መቀበያና
3ኛው ክፍል ለራሳቸውና ለቤተ ሰብእ አገልግሎት

በዚህ ሁኔታ በሰውና በእግዚአብሔር የተመሰገኑ ደጋግ ሰዎች ልጅ ሳይኖራቸው ብዙ ዘመናት አለፉ፡፡ ስለዚህም ኢያቄምና ሐና እግዚአብሔር ልጅ ቢሰጣቸው መላ ዘመኑ ቤተ እግዚአብሔርን የሚያገለግል እንደሚሆን ቃል ገብተው ተሳሉ፡፡
ከዚያም አንድ ቀን በኢየሩሳሌም በቤተ መቅደስ በዐል ሲከበር ኢያቄም ከጎረቤቶቹ ጋር መባዕ ይዞ በዓሉን ለማክበር ወደ ሚከምርበት ቤተ መቅደስ ኼደ፡፡ በጊዜው የነበረ ሊቀ ካህናት ይሳኮር ወይም ሮቤል ይበላል፡፡ ኢያቄም መባ ይዞ መምጣቱን አይቶ ወደ እርሱ ኼደና ኢያቄም ልጅ ሳይኖርህ፣ መኻን ሆነህ እንዴት ወደዚህ ትመጣለህ መባንስ እንዴት ታቀርባለህ እግዚአብሔር እኮ የመኻኖችን መባ አይቀበልም፣ አለና ከለከለው፡፡ ስለዚህ ኢያቄም በከፍተኛ ኃፍረትና ኅዘን ተመሰል፤ ዘፍ. 15፡27 ፤ 6፡1 ፤ ሳሙ. 1፡3-12፤

ኢያቄም በከፍተኛ ኀዘንና ኀፍረት ላይ እያለ ታላቅ ብርሃን የተጎናጸፈ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ ከፊቱ ቆመና እንዲህ አለው፡፡ "ኢያቄም እኔን በማየትህ አትፍራ፣ አትጨነቅ እኔ ጸሎትህ የተሰማ፣ ምጽዋትህ ቅድመ እግዚአብሔር የደረሰ የብዙዎቹን ማኅፀን ይዘጋል፤ ይከፈታልም፤ የጥንትዋ እናትህ ሣራ እስከ 80 ዓመት ዕድሜዋ ድረስ መኻን ነበረች፤ በኋላ የይስሐቅ እናት ሆነች፤ እንደዚሁም ራሄል የእግዚአብሔር ወዳጅ ሆና መኻን ነበረች፤ በኋላ የዮሴፍ እናት ሆነች፤

የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጆች የነበሩት የሳምሶንና የሳሙኤል እናቶች መኻኖች ነበሩ፤ በኋላ የእዚህ ታላላቅ ሰዎች እናቶች ሆኑ፡፡ መሳ.13፡1-24 ፤ 1ሳሙ. 1፡20 ፤

ስለዚህ አንተም ሚስትህ ሐና ሴት ልጅን ትወልድልሃለች፤ ስምዋንም "ማርያም"ብለህ ትጠራታለህ፤ ገና በእናትዋ ማኅፀን ሳለችም መንፈስ ቅዱስ ያድርባታል...በማለት አበሠረው፤ አሁንም ወደ ሐና ኼደና ሐና አይታው ስትደነግጥ አይቶ "ሐና አትፍሪ እኔን አይተሽ ሌላ መንፈስ ያየሽ አይመስልሽ፣ እኔ ጸሎትሽንና ምጽዋትሽን ከእግዚአብሔር ፊት የማቀርብ መልአክ ነኝና አሁንም የመጣሁት "ማርያም"የምትባል ልጅ የምትወልጂ መሆንሽን ልነግርሽ ነው"... በማለት አበሠራት፡፡ (the lost book of the Bible cha.1፡1, cha. 3)

በዚህም እውነት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአባትዋ ከኢያቄምና ከእናትዋ ከሐና ነሐሴ 7ቀን 5484ዓ.ዓ ተጸንሳ ግንቦት አንድ ቀን ተወለደች፤ ሦስት ዓመት ሲሆናት ወደ ቤተ መቅደስ ተወሰደች፤ ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ በቤተ መቅደስ ኖራ ዐሥራ አምስት ዓመት ሲሆናት በ5500ዓ.ዓ በብሥራተ መልአክ፤ በመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ጌታችንን ፀነሰች፡፡ በ5501ዓ.ዓ ልክ በ16ዓመት ዕድሜዋ ጌታችንን ወለደች፤ ጥር 21 ቀን 48 ዓመተ ምሕረት በ64 ዓመት ዕድሜዋ ዐረፈች፤

"ጊዜ ዕረፍታ ለሶልያና ወረደ ወልድ እምዲበ ልዕልና ጠሊሳን ንግሥ ለቤሃ ከደና"... ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ባረፈችበት ጊዜ ከላይ ከሰማይ ቃለ እግዚአብሔር ወረደና ወዲያው ልብሰ መንግስት አለበሳት ይለናል፤ ይህም አባባል የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍት ከሰው ልጆች ዕረፍት ሁሉ የተለየ የክብር፣ የሰላም... ዕረፍት መሆኑን ነው የሚያመላክተው፤

ቅዱሳን ሐዋርያት አባቶቻችን በጌቴሰማኒ መቃብር አዘጋጅተው ሊቀብሩአት በአጎበር ተሸክመው ሲኼዱ አይሁድ በምቀኝነት ተነሡና ካሁን በፊት ልጅዋ ተነሣ፣ ዐረገ...እያሉ ስማችንን እያጠፉ ናቸው፤ አሁን ደግሞ እናቱ ተነሣች፣ ዐረገች...እያሉ ስማችንን ሊያጠፉ አይደለም፤ ስለዚህ ኑ በእሳት እናቃጥላት ተባባሉና ከመካከላቸው ታውፊኒያ የሚባል በኃያልነቱ የሚመካ አይሁዳዊ ተነሣና ተራምዶ አጎበሩን እጥላለሁ ብሎ መያዣውን ሲጨብጭ መልአክ ሁለት እጁን ቀጣው ማለት በሰይፍ ቈራረጠው፡፡ ወዲያውም ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጣና ሐዋርያው ዮሐንስ ጨምሮ በደመና ነጥቆ ወደ ገነት ወሰዳትና በዕፀ ሕይወት ሥር አኖራት፡፡ ከዚያ በኋላ ዮሐንስ ሊመለስ ጓደኞቹ ሐዋርያት እንዴት ሆነች አሉና ጠይቁት፤ እሱም ከዕፀ ገነት ሥር አለች ቢላቸው ወደ ሰማያት ያረገችው በመላእክት ታጅባ ስለነበረ አሁንም ቅዱስ ያሬድ "አዕረግዋ መላእክት ውስተ ሰማያት" በማለት ይዘምራል፡፡

አባቶቻችን ቅዱሳን ሐዋርያት ወንድማችን ዮሐንስ አይቶ እኛ ሳናይ ቀረን በማለት አዝነው ነሐሴ 1ቀን 48ዓ.ም ጾም ጀመሩና ጾም በጀመሩ በ14ኛው ቀን ጌታ አምጥቶላቸው በጌቴሰማኒ ቀበሯት፡፡ በሦስተኛው ቀን ጌታችን ከሙታን ለይቶ አስነሥቶ ወደ ሰማያት ሲያሳርጋት ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ የተባለው ሐዋርያ ከሀገረ ስብከቱ በደመና ሊመለስ ተገለጸችለትና በመላእክት ታጅባ ስታርግ አይቶ አዘነ ተበሳጨ፤ ካሁን በፊት የጌታዬን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ሳላይ ቀርቼ ሳዝን ዛሬ ደግሞ ያንቺን ትንሣኤ ሳላይ መቅረቴ ነው አለ፡፡

እመቤታችንም አይዞህ አትዘን እነሱ ማለት ጓደኞችህ ሐዋርያት ትንሣኤንና ዕርገትን አላዩም፤ አንተ ግን አይተሃል፤ ስለዚህ ኺድና ተነሣች፣ ዐረገች ብለህ ንገራቸው ብላ የያዘችውን ሰበን ሰጥታ ሰደደችው፡፡ ከዚህ በኋላ ቶማስ ወደ ሐዋርያት ኼደና የእመቤታችን ነገር እንዴት ሆነ በማለት መየቃቸው፤ እነሱም ጌታ አምጥቶልን ቀበርናት አሉት፤ እሱም አረ ይህ ነገር አይመስልም ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር እንዴት ይሆናል?...በማለት ተከራከራቸው በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ አሳይሃለሁ ብሎ ደማውን ይዞ ተነሣ፤ መቃብሩን ቆፈረና ባዶ ሁኖ አገኘው፤ ምንድን ነው?...ብለው ሁሉም ሲጨነቁ ቶማስ ብድግ አለና "ወንድሞቼ ሆይ እኔ እኮ አታምኑኝም ብየ ነው እንጂ እመቤታችን ተነሥታ ወደ ሰማያት ዐርጋለች" ብሎ የሰጠችውን ሰበን ሰጣቸው እነሱም ለበረከት ተካፍለውታል፡፡

በዓመቱ በ49ዓመተ ምሕረት መሆኑ ነው ቶማስ ትንሣኤዋንና ዕርገትዋን አይቶ እኛ ሳናይ ቀረን ማለት ሐዋርያት እንደገና ነሐሴ 1ቀን ጾም ጀመሩ፤ አሁንም ሁለቱን ሱባኤ ሊፈጽሙ ጌታ አመጣላቸውና ራስዋን እመቤታችንን መንበር፤ ጴጥሮስን ተራዳኢ ቄስ እስጢፋኖስን ሠራኢ ዲያቆን አድርጎ ራሱ ቀድሶ አቁርቦአቸው መልሶ አሳርጓታል፡፡
ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጾሙን "ጾመ ፍልሰታ"ማለት እመቤታችን ወደ ሰማይ ያረገችበት በማለት ሕፃን ሽማግሌ ሳይባል፤ ሁሉም በአንድነት በመጾም የእመቤታችንን በዓለ ዕርገት ታስታውሳለች፤ ከላይ በአርእስቱ እንደተገለጸም ምሳሌውና ትንቢቱ የተፈፀመላት ድንግል ማርያም ሁሉን የሚችል አምላክ የእግዚአብሔር ቃለ ማደርያ

ያደረጋት፤ የልጅዋ አገልጋይ የሆነ አባትዋ ዳዊት በመሰንቆው እየዘመረ ከዚህ ከሚያለፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም ተሸገረች፤ ኼደች፣ ዐረገች…በማለት ትዘምራለች እግዚአብሔርን ታመሰግናለች፡፡

አሁንም ለዚህ የእመቤታችን በዓለ ዕርገት ያደረሰን አምላክ ክብር ምስጋና ይድረሰው አሜን፡፡